የካሳ አወሳሰን

በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል ለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ

ቢኒያም ዮሐንስ

(የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ)

የሰልጠናው አስፈላጊነት

- የጉዳት ኪሳራዎችን ከግዴታዎች ምንጭ ጋር በመለየት ካሳን መወሰን ለህግ ባለሙያ አስፈላጊ ተግባር በመሆኑ
- በተለያዩ መሰረታዊና የሥነ-ሥርዓት ህጎች ስለ ካሳ የተመለከቱትን ለመመልከት
- ካሳ ምንድን ነው የሚለው በህግ በግልጽ ትርጉም ባለመሰጠቱ - ለምሳሌ ባህር ዛፍ የተወሰደበት ሰው አላግባብ ተከሳሹ ወስዶ ስለሸጠው ግምት ይከፈለኝ ቢል የካሳ ክርክር ነውን? ተቆርጦ የተወሰደው ባህር ዛፉ በዓይነት ይመለስ ቢልስ ካሳ ወይስ የንብረት ክርክር?

1 በፍትሐ ብሄር ጉዳዮች የግዴታዎች ምንጭ

በህብረተሰብ ውስጥ በግለሰቦች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በአግባቡ ለመፍታት ሰላምን ለማስፈን ከሚያስችሉት ህጎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ያጠፉ የሚቀጡበትን እና የተበደሉ የሚካሱበትን የሚደነግጉ ሲሆኑ እነዚህንም የወንጀል እና የፍትሃብሄር ህጎች ተብለው ይከፈላሉ።

- የግዴታው ምንጭ ምንም ይሁን ምን፣ ማናቸውም የፍትሃብሄር ግዴታ አንድን ነገር ከማድረግ ካለማድረግ ወይም አንድን ተለይቶ የሚታወቅ ነገር ለሌላው ከማስረከብ ጋር የተያያዘ ነው።
- አብዛኞቹ የህግ ባለሙያዎች የፍትሐብሄራዊ ግዴታዎች ምንጭ ሁለት ናቸው፡- እነርሱም ውልና ከውል ውጭ ሃላፊነቶች ናቸው ሲሉ፣ አንዳንዶቹ ደገሞ የግዴታዎች ምንጭ ሶስት ናቸው፡ በህግ የሚጣሉ ግዴታዎች በተጨማሪነት የግዴታ ምንጭ ይሆናሉ፣ ከውል ውጭ ሃላፊነት የሚኖር ግዴታ እና በህግ የሚጣል ግዴታ የተለያዩ ናቸው በማለት ያስቀምጣሉ። አሰልጣኙ ሁለተኛውን ሀሳብ የሚጋራ ሲሆን፣በዚህ ዙሪያ ሰልጣኞች ሀሳብ ካላቸው ማንሳት ይችላሉ።

- ሀላፊነቶችን ከግዴታቸው ምንጭ አንፃር መለየቱ ለድርጊቱ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባውን የህግ ድንጋጌ ከመለየትና ለጉዳዮች አስፈላጊውን ዕልባት ከመስጠት አንፃር የራሱ የሆነ ፋይዳ ይኖረዋል።
- ለምሳሌ ባህር ዛፍ የተወሰደበት ሰው አላግባብ ተከሳሹ ወስዶ ስለሸጠው ግምት ይከፈለኝ ቢል የካሳ ክርክር ነውን? ተቆርጦ የተወሰደው ባህር ዛፉ በዓይነት ይመለስ ቢልስ ካሳ ወይስ የንብረት ክርክር? ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚደርስ ኪሳራስ ሊካስ የሚገባው በውል ህጉ መሰረት ነው ወይንስ ከውል ውጭ ሃላፊነቶችን በሚደነግገው የህጉ ክፍል የሚለውን ለመለየትና ለመወሰን ይረዳናል።

2 ካሳ አወሳሰን በተለያዩ ህጎች

- 2.1. በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011አንቀፅ 103 ጀምሮ በስራ ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሳ ሊከፈል እንደሚገባ ያዛሉ።
- ጊዜያዊ ጉዳት
- ዘላቂ ጉዳት - ዘላቂ ሙሉ
  - ዘላቂ ከፊል
- ሞት ሲከሰት ለባል ወይም ሚስት እና ልጆች ወይም ጥገኞች
- የህክምና ወጪ - በሀገር ውስጥ የሚሰጥ ህክምና ሲሆን?
  - በውጭ ሀገር የሚሰጥ ህክምና ሲሆን?
- ዘላቂ ሙሉ ለአካል ጉዳት ከሆነ ከህክምና ወጭ በተጨማሪ የሠራተኛው የዓመት ደመወዙ በአምስት ተባዝቶ ይከፈለዋል (አንቀጽ 109(3)(ሀ)

- 2.2 በንግድ ህጉ

3. **በንግድ ህግ** - ሰውና እቃ ስለሚÒÒዝበት ስርዓት የተደነገጉ ድንጋጌዎች አሉት።

- በየብስ ሰውን ስለማÒÒዝ የንግድ ህጉ ተፈጻሚ ሲሆን ዕቃን ስለማÒÒዝ የንግድ ህጉ ክፍል **በአዋጅ ቁጥር 547/99 ተሸVል**።

- ሰው ተሳፍሮ ሲሄድ ጉዳት ቢደርስበት በንግድ ህግ አንቀጽ 597(1) መሰረት ካሳው ከአርባ ሺህ ብር አይበልጥም።

- ንግድ ህግ አንቀጽ 599 የአጓዙ ጥፋት ወይም ጉድለት ካለ በአርባ ሺህ ብር ሳይወሰን በደረሰው ጉዳት ልክ ካሳ ሊወሰንበት ይችላል። (የሰበር መዝገብ ቁጥር 67973 ቅጽ 11)

- በንግድ ህግ ለጉዳቱ አÒዙ ሃላፊ ነው ሲል ነጋዴውን (ባለሀብቱን) ወይስ ሾፌሩን? ሃላፊ የሚሆነው ነጋዴው ነው ከተባለ ሾፌሩ ከውል ውጭ ሀላፊነት ሊጠየቅ ነው? እንዲህ ከሆነ ማን ከፍ ያለ ካሳን እንዲከፍል ይገደዳል?
- ከውል ውጭ ሃላፊነት የመኪናው ባለቤት በደረሰው ጉዳት ልክ ይከፍላል (አንቀጽ 2081) - ውል ወሰዶ በንግድ ህጉ አግባብ የሚያÒÒዝ ባለቤት ግን ከ40ሺህ ብር በላይ አይከፍልም ሲል ሁለቱ ህጎች እንዴት ይታረቃሉ? ፍትሐዊነቱስ?
- በየብስ (የሀገር ውስጥ ውሃን ጨምሮ) ዕቃ ስለሚÒÒዝበት ሁኔታ የንግድ ህጉ ተፈፃሚ አለመሆን እና አዋጅ ቁጥር 547/99 ለዚሁ ዓላማ ተፈፃሚ ስለመሆኑ፡

  - ዕቃ ከጠፋ ዕቃውን ማስረከብ በነበረበት ቦታ ባለው የገበያ ዋጋ (market value)(አንቀጽ 27(1))

  - ከዘገየ ከማÒÒዣ አገልግሎት ክፍያ ዋጋ ያልበለጠ (አንቀጽ 27(4))

  - ሆን ተብሎ ጥፋት ከተፈጸመ ከላይ የተገለጹት ደንቦች ተፈፃሚ አይሆኑም(አንቀጽ 32(1))

2.3 በውል ህግ

ውል በዝርዝር በተመለከተው አግባብ ሳይፈጸም ሲቀር፣ የጉዳት ኪሳራ ሲጠየቅ እና ካሳ የመክፈል ሃላፊነት አለበት ሲባል የሚከተሉትን መመርመር ያስፈልጋል።

2.1. ውሉ በራሱ የጉዳት ኪሳራ መጠን የተገለጸበት ነውን

- በፍ/ህ/ቁ. 1889 እና ተከታዮቹ መሰረት ተዋዋዮች ኪሳራውን አስቀድመው ኪሳራውን በውል ሊወስኑ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ፍርድ ቤቱ መቀጮውን በውሉ መሰረት ይወስናል።
- የፍትሐ ብሔር ክርክር በፍ/ሥ/ሥ/ህ.ቁ. 277፣ 278 መሰረት በዕርቅ ስምምነት ሲያልቅ ተዋዋዮች በስምምነቱ መሰረት ካልተፈጸመ መቀጮ እንዲከፈል የውሉ አካል አድርገው ያካትታሉ። ስለዚህ ኪሳራው ወይም መቀጮው እንዴት ይወሰናል - የሚከተሉትን የሥነ-ሥርዓት ጥያቄዎች ያስነሳል?
  - እርቅ ከጸደቀ ውጤቱ እንደፍርድ ስለሆነ ተገዶ ይፈጸማል። ስለዚህ ዕርቅ መቀጮ ያስፈልገዋልን?

- መቀጮ ተካቶ ሲመጣ ከስምምነቱ እንዲወጣ መደረግ አለበት ወይስ መቀጮው አብሮ መጽደቅ አለበት? ከመዋዋል ነጻነት አንጻር እንዴት ይታያል?
- ዕርቁ ከነመቀጮው ከጸደቀ ፍርዱ እንዴት ይፈጸማል? መቀጮው በአፈጻጸም ችሎቱ ሊታይ ይችላልን? ውል አፍራሹ ማነው የሚለው ማስረጃ መስማትም የሚያስፈልገው ከመሆኑ አንጻር አፈጻጸም ችሎት ፍሬ ነገር አጣርቶ መወሰን ይችላልን? በማስረጃ ተጣርቶ የሚፈጸም ፍርድ አለን?

➢ በውል ከተዋዋሉት በላይ ካሳ ለመወሰን የሚቻለው በፍ/ህ/ቁ. 1892(2) እንደተመለከተው ውሉ ያልተፈጸመው በአንዱ ወገን ጉልህ ቸልተኝነት ወይም ከባድ ጥፋት መሆኑን ማረጋገጥ ሲቻል ነው።

- ዳኞች መቀጫን ወይም ኪሳራን ተዋዋዮች ከተዋዋሉት በታች መቀነስ የሚችሉት በፍ/ህ/ቁ. 1893 እንደተመለከተው ውሉ በከፊል ከተፈጸመ ብቻ ነው።

2.2. የውሉ ዓይነትና ባህሪ በተዋዋዮች ኪሳራ አስቀድመው ለመዋዋል ይፈቅዳልን የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል።

- በብድር ውል በፍ/ህ/ቁ. 2489(1)(2) መሰረት ተዋዋዮች ኪሳራ ቢወስኑ የውሉ ቃል ፈራሽና ተፈፃሚነት የሌለው ነው።
- ስለሆነም ስለውሉ በህግ የተመለከቱ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን መመርመር ያስፈልጋል።
- ተዋዋዮች ኪሳራውን በውል ካልወሰኑ ወይም በህግ እንዲወስኑ ካልተፈቀደላቸው የደረሰውን ኪሳራ በማስረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ በህግ በተገቢው ሁኔታ መወሰን ያስፈልጋል።

4. ከውል ውጭ ሃላፊነት ካሳ የሚሰላበት ስርዓት

ከውል ውጭ የሚደርስ የጉዳት ኃላፊነትን በተመለከተ ህጋችን የጉዳት ዓይነቶችን ከመዘርዘሩ በስተቀር ስለጉዳት ትርጉም ያስቀመጠ ድንጋጌ አናገኝም። ሆኖም ስለጉዳት ከተለያዬ ድንጋጌዎች ከተሰጠው ትርጉም አንፃር ጉዳት በሰው ጥቅም ወይም ሀብት ላይ የሚደርስ ጉድለት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

- ካሳ ማለት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት አንድ ሰው በንብረቱ፣ በገንዘብ ጥቅሙ ወይም በሠውነቱ ላይ የደረሰ ጉዳት ማለት ነው።
- ዳኞች የጉዳት ኪሳራን አስመልክቶ የሚሰጧቸው መፍትሔ የጉዳዬችን ዓይነት መሰረት ያደረገ የገንዘብ ክፍያን ማዘዝ /Payment of money/፣ አንድ ተግባርን በግድ ማስፈፀም /Specific performance/ እና መብትን አረጋግጦ ማሳወቅ /Declaratory relief/ ሊሆኑ ይችላሉ።

- **<u>የጉዳት ዓይነቶችና የካሳ አከፋፈል ሥርዓታቸው</u>**
- **በሰው ጥቅም ወይም ሀብት ላይ የሚደርስ ኪሳራ ወይም ጉድለት በገንዘብ ሊተመን የሚችል ወይም ደግሞ ተምኖ ማስቀመቀጥ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ይህን መሰረት በማድረግም ሲከፈሉ**
- 2.2.1 **<u>ግልጽ የሆኑ ጉዳቶች</u>**/Material Damage/
- **ጉዳቱ በቀጥታ ንብረት ላይ የደረሰ ከሆነ በጉዳቱ ምክንያት ንብረቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከጥቅም ውጭ ከሆነ ይኸ ንብረት ያለውን ዋጋ የሚመለከት፣ ወይም አንድ ሰው በደረሰበት የአካል ጉዳት ሳቢያ ያወጣውን ገንዘብ ወይም የተቋረጠበትንም ሆነ ወደፊት የሚቋረጥበትን ጥቅም ይጨምራል። ግልፅ የሆኑ ጉዳቶች በአጭሩ በተጎጂው ላይ የደረሱ የገንዘብ ወይንም የአካል ጉዳቶችና ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ጉዳቶች ናችው። ግልፅ ጉዳቶች የደረሱ ወይንም ለወደፊቱ የሚደርሱ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ**

- <u>የደረሱ ጉዳቶች/Present Material Damage/</u>
- ይህ በተጎጅው ላይ በእርግጠኛነት የደረሰውን የገንዘብ ኪሳራ የሚመለከት ነው። የንብረት ጉዳት የደረሰበት ሰው በጉዳቱ ምክንያት የንብረቱ ዋጋ መቀነስ ወይም ሙሉ ለሙሉ ዋጋ ማጣት ሊደርስበት እና የሚያስገኘው ጥቅም ወይም ገቢ ሊቋረጥ የቻለውን በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳቱ በሰው አካል ላይ የደረሰ ከሆነ በጉዳቱ ምክንያት ለህክምና ያወጣውን እና ተያያዥነት ያላቸውን ወጭዎች ወይም በደረሰበት ጉዳት ሳቢያ ሥራ ባለመስራቱ ያጣውን ገቢ የሚጨምር ይሆናል።

- ለ. <u>ወደፊት የሚደርስ ጉዳት/Future Damage/</u>
- በንብረት ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ባለንብረቱ ወደፊት የሚያስገኘው ጥቅም ወይም ገቢ በመቋረጡ ወይም ጉዳቱ በሰው አካል ላይ የደረሰ ከሆነ በጉዳቱ ምክንያት ለወደፊቱ /ለተወሰነ ወይም በዘላቂነት/ ለህክምና እንደሚያወጣ <u>የተረጋገጠውን</u> እና ተያያዥነት ያላቸውን ወጭዎች ወይም በደረሰበት ጉዳት ሳቢያ ሥራ ሊሰራ ባለመቻሉ <u>ወደፊትም</u> ለያጣ የሚችለውን ገቢ ወይም ጉዳቱ የህይወት ማለፊን ያስከተለ ከሆነ በህግ መብት የተሰጣቸውን ሰዎች ያጡትን እና በእርግጠኝነት ወደፊት የሚያጡት የሚጨምር ይሆናል።

- **ግልጽ ለሆኑ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል ሥርዓት**
- ግልፅ የሆኑ ጉዳቶች ፣ የደረሱ ጉዳቶችም ሆኑ ለወደፊት የሚደርሱ ጉዳቶች፣ በተመለከተ ሁለት መሰረታዊ የሆኑ አከፋፈል ሥርዓት የሚከተል ነው። እነሱም የተመዛዘነ /የተመጣጠነ/ እና የማይመጣጠን የካሳ አከፋፈል ሥርዓቶች የሚባሉ ናቸው።
- የተመዛዘነ /የተመጣጠነ/ የካሳ አከፋፈል ሥርዓት
- / The equivalence Rule/
- ይህ የካሳ አከፋፈሉ ሥርዓት በተለይ ግልፅ ለሆኑ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል በጣም ጠቃሚ ነው። የፍ/ህ/ቁ 2091 ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ሆኖ የተገኘው ሰው ለተጎጅው የሚከፍለው ካሳ በተጎጅው ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን እንዳለበት ይደነግጋል። ከዚህም አንፃር በተጎጅው ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን መመርመር የሚቻልባቸው መንገዶች/ስልቶች/

- ሀ. <u>ተጎጅውን ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት አቋም/ሁኔታ መመለስ / Reinstatement/</u>:- በዚህ መንገድ ተጎጅውን ለመካስ የተጎጅውን ከጉዳቱ በፊት የነበረውን ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ በመኪናው ላይ የደረሰውን ጉዳት ማስጠገን ወይም ሙሉ ለሙሉ ወድሞ ከሆነ አንድ ዓይነት የሆነ ሌላ መኪና እንዲያገኝ በማድረግ መካስ የደረሰበትን ጉዳት ለማስወገድ ያስችላል።
- ለ. <u>በምትክ ዋጋ ስለመካስ / Exchange value</u>/:- በተጐጅው ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት የንብረቱ ዋጋ እንዲቀንስ የተደረገ ከሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነው ወገን ልዩነቱን እንዲከፍል በማድረግ መካስ መንገድ ነው። በዚህ ስልት ካሳ ለማስከፈል የንብረቱ ከጉዳቱ በፊት የነበረውን የገበያ ዋጋ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በሌላ ሁኔታ ደግሞ በጉዳቱ ምክንያት ዋጋው እንዲቀንስ የሆነው የንብረቱ የኪራይ ዋጋ ከሆነ ይኸው ከግንዛቤ ተወስዶ ካሳውን ማስላት ያስፈልጋል።

- ሐ. <u>ሊገኝ ይችል የነበረው ጥቅም በማመዛዘን ስለመካስ/ Utility</u>
- <u>Value</u>/:- በተጎጅው ላይ የደረሰው ጉዳት ትርፍ ወይም ጥቅም በማግኘት መብት ላይ ሲሆን ያጣው ትርፍ ተመዛዝኖ እንዲከፈለው ማድረግ ነው። ለምሳሌ፡- በንግድ ሥራ ተገቢ ያልሆነ ውድድር ምክንያት የደረሰ ጉዳት ወይም በመኪናው ላይ በደረሰ ጉዳት ያጣውን ማለትም ከገቢው ላይ ወጭዎቹ ተቀናንሶ የሚገኘውን የተጣራ ትርፍ መሰረት በማድረግ መካስ የደረሰበትን ጉዳት ለማስወገድ ያስችላል።
- በፍርድ ቤቶች በአብዛኛው ከሚቀርቡት ተጨባጭ ጉዳዬች አንፃር የተመዛዘነ /የተመጣጠነ / የካሳ አከፋፈል ሥርዓትን በሚመለከት በአካል ጉዳትና በሞት አደጋ የካሳ አከፋፈል ለማስላት የሚያስችሉ መሰረቶችን እንመለከታለን።

- ሀ.<u>ለአካል ጉዳት ካሳ አከፋፈል</u>
- በሰው አካል ላይ ለሚደርስ ጉዳት የሰው ልጅ አካል በገበያ ዋጋ የሚተመን ባለመሆኑ ካሳ በገንዘብ አስልቶ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ይሆናል። ስለሆነም በደረሰበት የአካል ክፍል ወይም ክፍሎች ጉዳት በደረሰ ጊዜ ሊከፈለው የሚገባውን ካሳ ለመወሰን ጉዳት በአካሉ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ያወጣውንና ያጣውን እንዲሁም ወደፊት የሚያወጣውንና ሊያጣ የሚችለውን ገንዘብ በማስላት ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆነው ወገን ለተጎጅው ካሳ እንዲከፍለው ይወሰናል።
- ስለሆነም ካሳውን ለማስላት ተጎጅው የተሰማራበት የሥራ ኣይነት ግምት ውስጥ ገብቶ ማመዛዘን ይጠይቃል።

- የአካል ጉዳት በደረሰ ጊዜ የወደፊት የጉዳት ካሳን ለመወሰን መከተል ያሉብን መንገዶች
- ሀ. የደረሰውን የጉዳት መጠን ማገናዘብ፡-
- ሙሉና ዘላቂ የአካል ጉዳት፡- የተጎጅውን መስራት ችሎታ መቶ በመቶ የሚገድብ ሲሆን ዘላቂ ማለት እስከ ተጎጂው የህይወት ፍፃሜ የሚቆይ መሆኑን ያመለክታል።
- ከፊልና ዘላቂ የአካል ጉዳት፡- የተጎጅውን የመስራት ችሎታ በከፊል የሚገድብ ሆኖ በተጎጂው ሰርቶ መኖር ሂደት ላይ እስከ እድሜ ልኩ ተፅዕኖ የሚያሳድር የጉዳት ዓይነት ነው።
- ጊዜያዊ የአክል ጉዳት፡- የሚድኑ የአካል ጉዳቶች እንደ ጊዜያዊ ህመም፣የሚድን ስብራት፤ቁስል፤...የመሳሰሉት የሚመለከት ሲሆን እስኪድን ድረስ ተጎጅው ስራውን እንዳይሰራ ሊከለክሉት የሚችሉ ናቸው።

- ስለሆነም የተጎዳው የአካል ክፍል ከተጐጂው የመስራት አቅምና ከስራው ጋር ያለው ግንኙነት በማገናዘብ የደረሰበት ጉዳት የሰራተኛውን የመስራት ችሎታ ይሰራ ከነበረው የሥራ ዓይነት/ዘርፍ/ አንፃር ያሳጠው ጠቀሜታን ከሚቀርቡ ማስረጃዎች ጋር አስተሳስሮ መፈተሽ ያስፈልጋል።
- በአንድ የእጅ ጣት መቆረጥ ላይ የደረሰ ጉዳትን ለማስረዳት በቀረበው የሐኪም ማስረጃ ከጠቅላላው አካል አንፃር 10% / አስር በመቶ/ የሚል ሊሆን ይችላል። ሆኖም ይህ የህክምና ማስረጃ ከተጎጅው ሙያ/ሥራ/ አንፃር የሚያስከትለውን የመስራት ችሎታ ማጣት መጠንን የሚገልጽ አይደለም።

- ለ. ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ የሰራተኛው ገቢ ወይም ደመወዝ ፡-
- በሰራተኛው ላይ በደረሰው የአካል ጉዳት ለተወሰነ ጊዜ በከፊል ወይም ሙሉና ዘላቂ በመሆን የተቋረጠበት ገቢ ወይም ደመወዝ የጉዳት ካሳውን ለማስላት ሌላው መሰረት ይሆናል።
- ሐ. የሠራተኛው በሥራ ላይ የሚቆይበት ዕድሜ፡-
  ወደፊት የሚደርስ ጉዳትን ለማስላት በጉዳቱ ወቅት ሠራተኛው ያለው ዕድሜ መነሻ በማድረግ ወደፊት በሥራ ላይ የሚቆይበት ቀሪ ዕድሜ ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል።
- በእኛ ሀገር ፍርድ ቤቶች የተጎጅውን ዕድሜ በተመለከተ የተዘበራረቀ አሰራር ይስተዋላል። እንዳንዶች የመንግስት የጡረታ እድሜን ሌሎች ደግሞ የሀገሪቱን የነፍስ ወከፍ እድሜ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባሉ። የትኛው አማራጭ ትክክል ይሆናል?

- በጉዳቱ ምክንያት የተከፈለ ወጪ እንደ ሆስፒታል የተመላለሰበት፣ ለመድሀኒት መግዣ፣ ለሰው ሰራሽ የአካል ምትክ እና የመሳሰሉት በቀላሉ በማስረጃ የሚረጋገጡ ሲሆን ጉዳቱ የዘላቂነት ባህሪ ሲኖረውና የተጎጂው የመስራት ሀቅም በሙሉ ወይም በከፍል ሲጓደል የጉዳት ክሳውን በመተመን ረገድ አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም። ስለዚህ ካሰው ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን አለበት ሲባል መታዬት የሚገባው በአጠቃላይ በተጎጅው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ መስራት ሀይል ቅነሳ /General Utility/ አንፃር እንጅ ልዬ ጫናና ቅነሳ መጠን/Special Utility/ ግምት ውስጥ በማስገባት አይሆንም። ይህም የሆነበት ምክንያት እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ሥራ ለመስራት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ እንደ ሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ነው።፤

- ለ. <u>የሞት አደጋ/ Mortal Accident/</u>
- በሞት አደጋ ምክንያት የሚከፈል ካሳ ለሌሎች አደጋዎች ወይም ጉዳቶች ከሚከፈለው የካሳ አከፋፈል ሥርዓት የተለዬ በመሆኑ ከውል ውጭ ስለሚደርስ አላፊነት የሚመለከቱ የህግ ድንጋጌዎች ብቻን በማየት ለመፈፀም ስለማይቻል ተዛማጅ ሕጐችን ማየትና መረዳትን ይጠይቃል።
- በፍ/ህ/ቁ.2095 በሞት አደጋ ምክንያት ካሳ እንዲከፈላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው የሚቹ ባል ወይም ሚስት፣ ወላጆቹና ልጆቹ ብቻ ሲሆኑ ለሞት አደጋው አላፊ የሆነው ወገን የሚከፍለው ካሳ ዓይነት ለምግብ ወይም መተዳደሪያ እንደሚከፈለው ጡረታ መልክና ዓይነት ስለመሆኑ የተመለከተ እና በፍ/ህ/ቁ. 2096 ደግሞ ሌሎች ሰዎች ምንም እንኳ ሚች ይረዳቸው እንደነበር ወይም ያስተዳድራቸው የነበረ ቢሆንም ካሳ የመጠየቅ መብት እንደሌላቸው ይደነግጋል።

- በፍ/ህ/ቁ.807፣በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 208 እና ተከታታይ ቁጥሮች እንደሚደነግጉት የቀለብ መስጠት ግዴታ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ሰው ሰርቶ ለመብላት የማይችል እና በችግር ላይ የወደቀ ሆኖ ሲገኝ እንዲሁም የቀለብ ተቀባዬን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የቀለብ ሰጭውን አቅም ማመዛዘን እንደሚያስፈልግ መረዳት ይቻላል።
  ከድንጋጌዎች የቀለብ አከፋፈል ሥርዓት በአንድ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ/ Lump Sum/ በመክፈል የሚፈፀም ሳይሆን በየወቅቱ/ Periodic/ መሆኑን የክፍያውም መጠን የመጨመር፣ የመቀነስ ወይም ክፍያው ሊቋረጥ እንደሚችል ያስገነዝባሉ።
- በሌላ በኩል ካሣ በጉዳት ምክንያት ሠው ያጣውን ጥቅም ወደነበረበት መመለስና ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ መመዘን እንዳለበት ሕጉ ከመደንገጉ አንጻር ካሣ ለማግኘትና ቀለብ ለመጠይቅ መስፈርቱ መለያየት አለበት። በሐግ በቀለብ መልክና ዓይነት የሚለው የካሣው አከፋፈልን እንጂ ከመነሻው ካሣ ለመጠየቅ ሊሆን አይባም የሚል ክርክር ስለሚቀርብና ሰበር ሰሚ ችሎትም በቀለብ ረገድ እንዲከፈል ከወሰነ በኋላ በሌሎች መዝገቦች ካሣ ጠያቂው ችግር ላይ የወደቀ ስለመሆኑ ሳያስረዳ ካሣ እንዲከፈለው ወስኗል። ለምሳሌ የሠበር መዝገብ ቁጥር 38117 ቅጽ 11...ስለሆነም ሁለቱ ክርክር ሰፍሮ ለሠልጣኞች ተገቢ ነው የሚሉትን አቋም እንዲይዙ እድል ቢሰጣቸው

- **<u>የማይመጣጠን/ Non- Equivalence/ የካሳ አከፋፈል ስርዓት</u>፡-**
- አጠቃላይ መርህ የሚከፈለው ካሳ/ኪሳራ/ በተበዳዬ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ በመመዘን ሲሆን የዚህ መርህ የተለዬ ሁኔታዎችን/ Exceptions/ የሚያካትተው የካሳ አከፋፈል የማይመጣጠን የካሳ አከፋፈል ሥርዓት ይባላል። ይህን የካሳ አከፋፈል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተበዳዬ ጥፋትን እና ርትዕን መሰረት ያደረጉ በሚል መመደብ ይቻላል።
- 1 የተበዳዬ ጥፋት፡- የተበዳዬ ወይም የካሳ ጠያቂው ጥፋት የሚወሰነውን የካሳ መጠን ለመቀነስ ምክንያት የሚሆነው ካሳ ጠያቂው ለደረሰበት ጉዳት የራሱ አስተዋጾኦ ያለበት ከሆነ ነው።

- የፍ/ህ/ቁ. 2098/2/ ተበዳዬ ላይ የደረሰው ጉዳት የራሱ የተበዳዩ ከፊል አስተዋፆኦ ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ የሚከፈለው ካሳም በከፊል እንደሚሆን ይደነግጋል። ስለሆነም በከፍል ካሳውን ለመወሰን የአካባቢ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ በተለይም የተበዳዬን የጥፋት መጠን በማመዛዘን በመደበኛ ሁኔታዎች ሊከፈለው ከሚገባው የካሳ መጠን ላይ በመቀነስ ሊሆን ይገባል።

- 2 ርዕትን መሰረት በማድረግ ካሳ የሚወሰንባቸው ልዩ ሁኔታዎች፡-
- በሕግ ላይ የተቀመጡ ሁኔታዎች በጥብቅ መከተል ሣያስፈልግ ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚሰጥ ውሳኔ
- /Justice without law/ ነው። ርዕትን መሰረት በማድረግ ካሳ የሚወሰንባቸው ልዩ ሁኔታዎች፡-
- ሀ. ድርጊቱ ጥፋት መሆኑን ባለማወቅ የደረሰ ጉዳት:- የሥራውን/ድርጊቱን/ ጥፋት ለመገመት የማይችል ሰው እንደ ሕጻን ወይም አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ፣ ወይም አእምሮው የጎደለው ሰው የሚፈፅመው ድርጊት አላፊነትን ሲያመጣ ዳኞች አላፊ በአላፊነት የተጐጅውንና በአላፊነት የሚጠየቀውን ወገን የሀብት መጠን በማመዛዘን እንዲሁም በአላፊነት የሚጠየቀው ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት በማመዛዘን ርትዕን መሠረት አድርገው ሊወስኑ እንደደሚችሉ የፍ/ህ/ቁ. 2099 ይደነግጋል።

- ለ.በበላይ ጥፋት ምክንያት የሚፈፀም ጥፋት፡- በአስተዳደራዊ ወይም በወታደራዊ ተቋማት ያለውን የበላይና የበታች ሠራተኛ መንግስታዊ ግንኙነት/Public relationship/የሚመለከት ነው። የበታች ሠራተኛው የበላይ አለቃው ትዕዛዝ ሕገ ወጥነትን እየተረዳ በተለይ የበላይ አለቃው ትዕዛዙን የመስጠት ሥልጣን ወይም ችሎታ የሌለውና ትዕዛዙም ሕገወጥ የወንጀል ተግባር መሆኑን እያወቀ ይህን ትዕዛዝ የፈፀመ የበታች ሰራተኛ ጥፋተኛ ነው። የፍ/ህ/ቁ. 2036 ይመለከቷል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ዳኞች ለተጐጅው የሚከፈለውን ካሳ የበታች ሰራተኛው የመታዘዙን ተገቢነት ማነስ ማደጉን በማመዛዘን ማለትም በትዕዛዝ ሰጪውና ተቀባዩ መካከል የነበረው ሁኔታዎችና የበታች ሠራተኛውን ሐሳብ በሚገባ አመዛዝነው ሊቀንሱት እንደሚችሉ የፍ/ህ/ቁ. 2100 ይደነግጋል።

- ሐ.ይደርሳል ተብሎ ሊታሰብ የማይችል ጉዳት፡- ሊታሰቡ በማይችሉ አጋጣሚዎች ምክንያት የደረሰው ጉዳት እስከዚህ ከፍ ያለ ነገር ያስከትላል ተብሎ በአዕምሮ ግምት ሊታሰብ የማይችል እንደነበረ የታወቀ ሲሆን፤ የርዕትዕ ሁኔታ የሚስገድድ በሆነ ጊዜ ዳኖች ውሳኔያቸው ፍትሀዊነት የጎደለው እንዳይሆን የመክፈል ግዴታ ያለበትንና የተጎጅውን ሁኔታ በማገናዘብ ርዕትን መሰረት በማድረግ ለተጐጅው የሚከፈለውን ካሳ መቀነስ እንደሚችሉ የፍ/ህ/ቁ. 2101/1/ ይደነግጋል። የካሳ መቀነሱ ደንብ ሆነ ተብሎ ለተደረገ የጥፋት ድርጊት ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 2 ያስገነዝባል።

- መ. ስለግምት አስቸጋሪነት፡- በአንዳንድ ሁኔታዎች በተጐጅው ላይ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ ሆኖ የጉዳቱን መጠን ማስላት እጅግ በጣም አስቸጋሪ ወይም የጉዳቱን መጠን ማስላት የማይቻልበት ሁኔታ ዳኞች ነገሮችን ተራ ሁኔታና ተጎጅው ያደረገውን ጥንቃቄ እንዲሁም የአካባቢውን ልምድ መሰረት በማድረግ ዳኞች የጉዳቱን መጠን በመገመት በርትዕ ካሳውን መወሰን እንዳለባቸው የፍ/ህ/ቁ.2102/1/ ይደነግጋል።

- በርትዕ ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮች

  - ህፃን ሲጎዳ ወይም ሲሞት
  - በሀገሪቱ ካለው ከዕድሜ ጣሪያ በላይ የኖረ ሰው ጉዳት ሲደርስበት
  - የተጎጂው ገቢ gሚ አለመሆን
  - የስራ ቀናት gሚ አለመሆን
  - ማስረጃው ወይም ምስክሮች ስለ ገቢው ያስረዱት ግምታዊ መሆን
  - ቃጠሎ ቢኖርና የሱቅ ዕቃ ወይም የቤት ዕቃ ሙሉ ዝርዝርን ማስረዳት ሳይቻል ሲቀር

- ርትዕ መሰረት ተደርጎ ሲወሰን የዳኛው ግምት ብቻ እንዳይሆን **ርትዕን ሚዛናዊ** ለማድረግ፡

  - በአካባቢው ሁኔታ ወደፊት ሊሰማራ የሚችልበት ሁኔታን ማየት - ለምሳሌ የገጠር ነዋሪ ከሆነና ያልተማረ ከሆነ በግብርና ሊሰማራ እንደሚችል በማሰብ መወሰን

  - የሚማር ከሆነ ለምሳሌ የመንግስት ሰራተኛ አማካይ ደመወዝ

  - በአካባቢው ተመሳሳይ ስራ የሚያስገኘውን አማካይ ገቢ በማጣራት

  - ተመሳሳይ የንግድ ዘርፍ ያለውን ሃብት በማመዛዘን

- ሠ.አስፈላጊ ሁኔታ፡- ማንም ሰው ጥፋት ሳያደርግ ራሱን ለማዳን፣ ወይም ሌሎችን ከጉዳት ወይም ከድንገተኛ አደጋ ለማዳን ሲል በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ዳኞች አድራጊው የሚከፍለውን የካሳ ገንዘብ ልክ በርትዕ እንደሚወስኑ የፍ/ህ/ቁ. 2103 ይደነግጋል። አስገዳጅ ድንጋጌ ነው።
-
- ረ. የተቀጣሪ ሠራተኛ ሐላፊነት፡- የመንግስት፣የግል ድርጅት፣ወይም በሌላ ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ ጥፋት ከፈፀመና በጥፋቱም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ ከሆነ ሠራተኛው ለተጎጅው የሚከፍለውን ካሳ በሙሉ ወይም በከፊል ቀጣሪው መንግስት፣ድርጅት ወይም አሰሪው ግለሰብ እንዲከፍል ዳኞች ለመወሰን እንደሚችሉ በዚህን ጊዜ የተሰራውን ጥፋት ከባድነት እና አድራጊው ጥፋቱን ሲሰራ የተሰጡትን ሥራዎች አብልጦ ለመፈጸም ሲል የነበረውን ፈቃድ መገመት እንዳለባቸው የፍ/ህ/ቁ.2157 ይደነግጋል።
- ሆኖም ግን ሠራተኛው አላፊነት ያመጣበትን የጥፋት ድርጊት የፈፀመው አስቦ ከሆነ ወይም በፈፀመው የጥፋት ድርጊት በወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ በካሳ አከፋፈሉ ላይ ሙሉ አላፊ እንደሚሆን የፍ/ህ/ቁ. 2159 ያስገነዝባል።

- ወደፊት የሚደርስ ግን የተረጋገጠ ጉዳት (future damage)

  እንዴት ይሰላል? gሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት ነገር ግን ጉዳቱ ገቢው ላይ ለውጥ ካላመጣ ካሳው እንዴት ይሰላል? የሠውነት ጉዳት የካሳ ተመኑ ምን ያህል ነው? gሚ የአካል ጉዳት በ% ሲገለጽ ከመስራት አቅም ማነስ ጋር ያለው ቁርኝት ምን ያህል ነው? gሚ የአካል ጉዳት 100% ሳይሆን ገቢው ግን 100% ቢgረጥ ካሳው እንዴት ማስላት ይቻላል?

- የኢትዮጵያ የዕድሜ ጣሪያውን ያለፈ ሰው ጉዳት ቢደርስበት ካሳው እንዴት ይሰላል?

- ተጎጂ ሲሞት ወራሾች በአንቀጽ 2095 መሰረት በመተዳደሪያ መልክና ዓይነት ካሳ ያገኛሉ። ይህ ማለት በቀለብ ረገድ በቤተሰብ ህጉ የተመለከተውን ስርዓት መከተል ይገባል ማለት ነው? የቤተሰብ ህጉ ቀለብ ለመጠየቅ ቀለብ ፈላጊ (needy) መሆን ያስፈልጋል። አባታቸው የሞተባቸው ልጆች ወይም ልጃቸውን በሞት ያጡ ወላጆች ካሳ ለመጠየቅ ቀለብ ፈላጊ ወይም መተዳደሪያ ገንዘብ የሌላቸው መሆን አለበት ማለት ነው?

- በቀለብ ረገድ የሚለው ከካሳ ተመጣጣኝነት (በደረሰው ጉዳት ልክ ወይም በተgረጠው ጥቅም ልክ) መርህ አንፃር እንዴት ይታያል? የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንድ ጊዜ ቀለብ ፈላጊ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት ያለ ሲሆን በሌላ ጊዜ ቅጽ 11 ላይ ልጃቸው መሞቱ ብቻ ካሳ ያስፈልጋቸዋል በማለት ውሳኔ ሰጥ~ል። የትኛው አgም ተገቢ ነው?
- ልጆች አስከ ስንት ዓመታቸው ድረስ በቀለብ ረገድ ክፍያ ይገባቸዋል? 18 ዓመት በ=ላ ትምህርት የቀጠለ ልጅ? ከ18 ዓመት በ=ላ ትምህርት ከቀጠሉ 2ኛ ክስ ቢያቀርቡ ውጤቱ ከይርጋ እና splitting of claims አèያ ምን ይሆናል?

- ለስራ ያልደረሰ ገቢ የሌለው ህጻን ልጅ በጉዳት ምክንያት ቢሞት ለወላጆቹ ካሳ እንዴት ይወሰናል?
- ተቀጣሪ ሠራተኛ እና የስራው ባለቤት ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ አርሶ አደር ጉዳት ቢደረስበት በካሳ አሰላሉ ላይ ልዩነት አለውን? ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ ጉዳት ሲደርስበት የንግዱ ወይም የመሬቱ ሙሉ ትርፍና ውጤት ወይስ ተጎጂውን ለመተካት ሰው ቢቀጠር ያስከተለው ወጪ ወይስ ቢያከራዩት የሚቀረው ጥቅም ልዩነት? የትኛው ፍትሐዊ ነው?
- ካሳ በፍ/ህ/ቁ. 2102 መሰረት በርትዕ ይወሰናል። ርትዕ ማለት ዳኞች የሚያስቡት የካሳ መጠን ማለት ነው? ይህ ከሆነ ከዳኛ ዳኛ ይገባዋል ብሎ የሚያስበው ካሳ መጠን አይለያይምን? Arbitrary ውሳኔ አይሆንምን - ከፍርድ ተገማችነት አèያ እንዴት ይታያል?

- ካሳ personal ነው። በግል የደረሰበት ጉዳት ተመዛዝኖ ይከፈለዋል። ከዚህ መርህ አèያ የሞራል ወይም የህሊና ጉዳት ካሳ እንዴት መወሰን አለበት? ሁለት እና ከዚህ በላይ ተጎጂ ሲኖር በፍ/ህ/ቁ. 2113 መሰረት ከአንድ ሺህ ብር በላይ ሊከፈል አይገባም ተብሎ በሰበር ችሎት መወሰኑ ተገቢ ነውን?
- በንብረት ላይ ጉዳት ካሳ የሚሰላበት ስርዓት - በየብስ (የሀገር ውስጥ ውሃን ጨምሮ) ዕቃ ስለሚÒÒዝበት ሁኔታ የንግድ ህጉ ተፈፃሚ አለመሆን እና አዋጅ ቁጥር 547/99 ለዚሁ ዓላማ ተፈፃሚ ስለመሆኑ - ዕቃ ከጠፋ ዕቃውን ማስረከብ በነበረበት ቦታ ባለው የገበያ ዋጋ (market value)(አንቀጽ 27(1))

  - ከዘገየ ከማÒÒዣ አገልግሎት ክፍያ ዋጋ ያልበለጠ (አንቀጽ 27(4))

  - ሆን ተብሎ ጥፋት ከተፈጸመ ከላይ የተገለጹት ደንቦች ተፈፃሚ አይሆኑም(አንቀጽ 32(1))
- በመኪና ላይ ጉዳት ሲደርስ ገቢዎች ላይ ገቢ ብሎ ባሳወቀው እና በማስረጃ የመኪናው ዕለታዊ ወይም ወርሃዊ ገቢ በተረጋገጠው መካከል ልዩነት ሲኖር የትኛው ሊወሰድ ይገባል?

- ለስራ ያልደረሰ ገቢ የሌለው ህጻን ልጅ በጉዳት ምክንያት ቢሞት ለወላጆቹ ካሳ እንዴት ይወሰናል?
- ተቀጣሪ ሠራተኛ እና የስራው ባለቤት ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ አርሶ አደር ጉዳት ቢደረስበት በካሳ አሰላሉ ላይ ልዩነት አለውን? ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ ጉዳት ሲደርስበት የንግዱ ወይም የመሬቱ ሙሉ ትርፍና ውጤት ወይስ ተጎጂውን ለመተካት ሰው ቢቀጠር ያስከተለው ወጪ ወይስ ቢያከራዩት የሚቀረው ጥቅም ልዩነት? የትኛው ፍትሐዊ ነው?
- ካሳ በፍ/ህ/ቁ. 2102 መሰረት በርትዕ ይወሰናል። ርትዕ ማለት ዳኞች የሚያስቡት የካሳ መጠን ማለት ነው? ይህ ከሆነ ከዳኛ ዳኛ ይገባዋል ብሎ የሚያስበው ካሳ መጠን አይለያይምን? Arbitrary ውሳኔ አይሆንምን - ከፍርድ ተገማችነት አèያ እንዴት ይታያል?

- በአሠሪና ሠራተኛ ህግ በስራ ላይ የደረሠ ጉዳት የካሳ ተመጣጣኝነት ዓላማን የያዘ ነውን?
- አንቀጽ 96(3) አሠሪው ጥፋት ካለበት ሠራተኛው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ካሳ የመጠየቅ መብቱን አይነኩበትም።
- የአሠሪው ጥፋት አለ የሚባለው መቼ ነው ?
- በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 ጥፋት ያለበት አሠሪ ከሆነ በሌላ ህግም ሊጠየቅ ይችላል ሲል የስራ ውል ግንኙነት ስላላቸው በውል ህግ ማለቱ ነው ወይስ ከውል ውጭ ሃላፊነት?
- በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ሰራተኛው ካገኘው ካሳ በተጨማሪ በሌላ ህግ እንደገና ካሳ ሲወሰንለት ከካሳ ተመጣጣኝነት መርህ አንፃር እንዴት ይታያል

- ቀድሞ የተከፈለው ይቀነሳል ወይስ በሌላው ህግ የከሳው ስሌት ተሰልቶ ሙሉው ይከፈለዋል?
- የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንዱን ህግ መርጦ ከከሰሰ ሁለተኛ ሊከስ አይገባም በማለት ወስኗል። ውሳኔው ተገቢና ህጋዊ ነውን? በሌላ ህግ ሲከስ ስሌቱ 20ሺህ ብር ቢያገኝ ነገር ግን በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ በደመወዙ ስሌት 40ሺህ ብር የሚያገኝ ቢሆን ቀሪው 20ሺህ ብር ሳይከስ ይቀራል ማለት ነው? በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ እና በሌላ ህግ አጣምሮ በአንድ ክስ ቢያቀርብ ከሰበር ውሳኔ አንፃር እንዴት ይታያል?

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ንግድ ህጉን በተመለከተ

    1.1. በንግድ ህጉ ካሳ የሚሰላበት ስርዓት ያልተመለከተ ከመሆኑ አንጻር የካሳ መጠኑ በየትኛው ህግ ሊሰላ ይገባል? ለምን?

    1.2. አÒኞ የመኪናው ባለቤት ነጋዴው ወይስ ሾፌሩ ወይስ ሁለቱም?

    1.3. ከውል ውጭ ሃላፊነት በፍትሐ ብሔር ህግ ከተሰላ የሞራል ካሳን፣ ለወደፊት የሚደርስ(future damage) ካሳን ያካትታልን?

    1.4. የደረሰበት ጉዳት ካሳው ሲሰላ ከአርባ ሺህ ብር ከበለጠ ልዩነቱን በሌላ ህግ ሊጠየቅ ይገባልን? አርባ ሺህ ብር ብቻ የሚወሰን ከሆነ ከካሳ ተመዛዛኝነት ወይም ተመጣጣኝነት መርህ አንፃር እንዴት ይታያል?

1.5. ውል ከአÒዙ ጋር ወስዶ በደህና ለመድረስ የተሳፈረው ሰው ሲጎዳ አርባ ሺህ ብር ብቻ የሚከፈል ከሆነ እና ከውል ውጭ ሃላፊነት ያለበት ሰው ግን በደረሰው ጉዳት ልክ የሚከፍል ከሆነ የህጉ ሚዛንና ፍትሐዊነት እንዴት ይታያል?

1.6. በንግድ ህጉ አንቀጽ 599 ላይ ያለው የአÒዙ ጥፋት ወይም ጉድለት የሚለው የነጋዴውን ጥፋት ወይስ የሾፌሩ ጥፋት ማለት ነው? ነጋዴው መኪናውን ራሱ የማያሽከረክር ከሆነ እንዴት ጉድለት አለበት ሊባል ይችላል

2. ከውል ውጭ ሃላፊነት አጥፊ ሳይሆን ሃላፊ (strict liability) የሚሆኑ እንዳሉ ተመልክቷል።(ከፍ/ህ/ቁ. 2066 እና ተከታዮቹ)

2.1. እንዚህ ሰዎች ሃላፊነት የሚኖርባቸው (ለምሳሌ በመኪና ባለሃብት) ሾፌሩ ጥፋት ሲኖርበት ነው ወይስ በማናቸውም ሁኔታ?

2.2. በፍ/ህ/ቁ. 2098 የተበዳይ ከፊል ጥፋት ካለ ካሳው እንደሚቀነስ ይደነግጋል። ጥፋቱ ሙሉ በሙሉ የተጎጂው ከሆነ በተለይ አጥፊ ሳይሆኑ ሃላፊ ለሚሆኑ ሰዎች ተፈጻሚነት አለውን?

2.3. ተፈጻሚነት አለው ከተባለ አጥፊ ሳይሆኑ ሃላፊነት አለባቸው ከሚለው መርህ ጋር ተቃርኖ አይኖረውም ?

3. የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 83 የካሳ ጥያቄ የቀረበውን የገንዘብ ልክ በሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ያልተካደ ነገር እንደታመነ ይቆጠራል ይላል።

3.1. ይህ ማለት በካሳ ክርክር ተከሳሹ ምንም የሚክደው ነገር የሚጠበቅበት የለም ማለት ነው? ለካሳው ሃላፊነት የለብኝም በማለት መካድ አይጠበቅበትምን?

3.2. የካሳ መጠኑን ለማስላት መሰረት የሆኑ የተጎጂው ዕድሜ፣ የዕድሜ ጣሪያ፣ የገቢ መጠን፣ ተጎጂው ሲሰራ የነበረው ስራን በተመለከተ ተከሳሹ ባይክድ ከሳሹ ማስረዳት አለበት ማለት ነው ወይስ ድምር መጠኑን መካድ አይጠበቅበትም እንጂ ድምሩን ለማስላት ያሉትን ፍሬ ነገሮች መካድ አለበት ማለት ነው?

3.3. የካሳው ክርክር ተከሳሽ በሌለበት ሲሆንስ ውጤት ምን ይሆናል

4.2. የህሊና ጉዳት (የሞራል ካሳ) - በጉዳቱ ምክንያት የስሜት መጎዳት ካለ ስሜትን በገንዘብ መተመን አስቸጋሪ ነው ። ግን ህግ አውጪው አንድ ሺህ ብር እንዲከፈል የገንዘብ መጠኑን ተምኗል።

- ካሳ personal ነው። በግል የደረሰበት ጉዳት ተመዛዝኖ ይከፈለዋል። ከዚህ መርህ አèያ የሞራል ወይም የህሊና ጉዳት ካሳ እንዴት መወሰን አለበት?
- የሞራል ካሳ በቸልተኝነት ለደረሰ ጉዳት ይከፈላልን ? አንቀጽ 2106 እና 2113
- የፍ/ህ/ቁ. 2116(3) በማናቸውም ምክንያት ከአንድ ሺህ ብር አይበልጥም የሚለው ለተጎጂው ወይስ ለቤተሰቡ፤ አራት ልጅ ያለው አባት ሲሞትና አንድ ልጅ ያለው አባት ሲሞት አራቱ ልጆች እያንዳንዳቸው 250 ብር ያገኙሉ፤ አንዱ ልጅ አንድ ሺህ ያገኛል ማለት የስሜት መጎዳት ልዩነት እንዳለ የሚያሳይ አይደለምን?
- Material damage ለእያንዳንዱ ልጅ በግል ወሰኖ የሞራል ጉዳት ግን ለቤተሰቡ መወሰን ተገቢ ነውን? ከአንድ ሺህ ብር በላይ ሊከፈል አይገባም ተብሎ በሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 69428 ቅጽ 13 መወሰኑ ተገቢ ነውን?
- በቅጂና ተዛማጅ አዋጅ ቁጥር 410/96 አንቀጽ 34(4) መሰረት የሞራል ካሳ ከአንድ መቶ ሺህ ብር ያላነሰ

- ወደፊት የሚደርስ ግን የተረጋገጠ ጉዳት (future damage) እንዴት ይሰላል?
- gሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት ነገር ግን ጉዳቱ ገቢው ላይ ለውጥ ካላመጣ ካሳው እንዴት ይሰላል? የሠውነት ጉዳት የካሳ ተመኑ ምን ያህል ነው?
- gሚ የአካል ጉዳት በ% ሲገለጽ ከመሰራት አቅም ማነስ ጋር ያለው ቁርኝት ምን ያህል ነው? gሚ የአካል ጉዳት 100% ሳይሆን ገቢው ግን 100% ቢgረጥ ካሳው እንዴት ማስላት ይቻላል?
- የኢትዮጵያ የዕድሜ ጣሪያውን ያለፈ ሰው ጉዳት ቢደርስበት ካሳው እንዴት ይሰላል?
- ተጎጂ ሲሞት ወራሾች በአንቀጽ 2095 መሰረት በመተዳደሪያ መልክና ዓይነት ካሳ ያገኛሉ። ይህ ማለት በቀለብ ረገድ በቤተሰብ ህጉ የተመለከተውን ስርዓት መከተል ይገባል ማለት ነው? የቤተሰብ ህጉ ቀለብ ለመጠየቅ ቀለብ ፈላጊ (needy) መሆን ያስፈልጋል። አባታቸው የሞተባቸው ልጆች ወይም ልጃቸውን በሞት ያጡ ወላጆች ካሳ ለመጠየቅ ቀለብ ፈላጊ ወይም መተዳደሪያ ገንዘብ የሌላቸው መሆን አለበት ማለት ነው?

- በቀለብ ረገድ የሚለው ከካሳ ተመጣጣኝነት (በደረሰው ጉዳት ልክ ወይም በተgረጠው ጥቅም ልክ) መርህ አንፃር እንዴት ይታያል? የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አንድ ጊዜ ቀለብ ፈላጊ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት ያለ ሲሆን በሌላ ጊዜ ቅጽ 11 ላይ ልጃቸው መሞቱ ብቻ ካሳ ያስፈልጋቸዋል በማለት ውሳኔ ሰጥ~ል። የትኛው አgም ተገቢ ነው?
- ልጆች አስከ ስንት ዓመታቸው ድረስ በቀለብ ረገድ ክፍያ ይገባቸዋል? 18 ዓመት በ=ላ ትምህርት የቀጠለ ልጅ? ከ18 ዓመት በ=ላ ትምህርት ከቀጠሉ 2ኛ ክስ ቢያቀርቡ ውጤቱ ከይርጋ እና splitting of claims አèያ ምን ይሆናል ወይስ በቀለብ መልክ ስለሆነ የቀለበ መጠን ሊሻሻል ይችላል የሚለው የቤተሰብ ህግ ይገዛዋል ?(የሰበር መዝገብ ቁጥር 50225 ቅጽ -10)

- ለስራ ያልደረሰ ገቢ የሌለው ህጻን ልጅ በጉዳት ምክንያት ቢሞት ለወላጆቹ ካሳ እንዴት ይወሰናል? (የሰበር መዝገብ ቁጥር 38117 - ቅጽ - 11)
- ተቀጣሪ ሠራተኛ እና የስራው ባለቤት ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ አርሶ አደር ጉዳት ቢደረስበት በካሳ አሰላሉ ላይ ልዩነት አለውን? ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ ጉዳት ሲደርስበት የንግዱ ወይም የመሬቱ ሙሉ ትርፍና ውጤት ወይስ ተጎጂውን ለመተካት ሰው ቢቀጠር ያስከተለው ወጪ ወይስ ቢያከራዩት የሚቀረው ጥቅም ልዩነት? የትኛው ፍትሐዊ ነው?
- በሰብል ጉዳት ደርሶ ኪሳራ ሲጠየቅ 1174(3) በተሰበሰበ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልተጠየቀ የመጠየቅ መብቱን ያጣል ይላል። የይርጋ ጽንሰ-ሃሳብ ነውን ?
- በመሬት ላይ የደረሰ ጉዳት እንዴት ይሰላል ? በምስክር፣ በባለሙያ ወይስ በአካባቢው ሽማግሌ ?
- ካሳ በፍ/ህ/ቁ. 2102 መሰረት በርትዕ ይወሰናል። ርትዕ ማለት ዳኞች የሚያስቡት የካሳ መጠን ማለት ነው? ይህ ከሆነ ከዳኛ ዳኛ ይገባዋል ብሎ የሚያስበው ካሳ መጠን አይለያይምን? Arbitrary ውሳኔ አይሆንምን - ከፍርድ ተገማችነት አèያ እንዴት ይታያል?

- ለስራ ያልደረሰ ገቢ የሌለው ህጻን ልጅ በጉዳት ምክንያት ቢሞት ለወላጆቹ ካሳ እንዴት ይወሰናል?
- ተቀጣሪ ሠራተኛ እና የስራው ባለቤት ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ አርሶ አደር ጉዳት ቢደረስበት በካሳ አሰላሉ ላይ ልዩነት አለውን? ነጋዴው ወይም ባለመሬቱ ጉዳት ሲደርስበት የንግዱ ወይም የመሬቱ ሙሉ ትርፍና ውጤት ወይስ ተጎጂውን ለመተካት ሰው ቢቀጠር ያስከተለው ወጪ ወይስ ቢያከራዩት የሚቀረው ጥቅም ልዩነት? የትኛው ፍትሐዊ ነው?
- ካሳ በፍ/ህ/ቁ. 2102 መሰረት በርትዕ ይወሰናል። ርትዕ ማለት ዳኞች የሚያስቡት የካሳ መጠን ማለት ነው? ይህ ከሆነ ከዳኛ ዳኛ ይገባዋል ብሎ የሚያስበው ካሳ መጠን አይለያይምን? Arbitrary ውሳኔ አይሆንምን - ከፍርድ ተገማችነት አèያ እንዴት ይታያል? (የሰበር መዝገብ ቁጥር 16270 ቅጽ -3፣ የሰበር መዝገብ ቁጥር 64590 -ቅጽ - 11)

  - የሰበር መዝገብ ቁጥር 79794 - ቅጽ 15 - የፍ/ህ/ቁ. 2102 በውል አፈጻጸም ክርክርም ተፈጻሚ ስለመሆኑ

ፀሚ የአካል ጉዳቱ ቀጥተኛ የጥቅም መቀነስ ባላስከተለበት ሁኔታ

- በፍ/ህ/ቁ. 2099 መሰረት ድርጊቱ ጥፋት መሆኑን ባለማወቅ የደረሰ ጉዳት

- በፍ/ህ/ቁ. 2100 መሰረት በበላይ ትዕዛዝ (በዲሲፕሊን ወይም በታዛዥነት) ምክንያት የሚፈጸም ጥፋት

- በፍ/ህ/ቁ. 2101 መሰረት ይደርሳል ተብሎ ሊታሰብ የማይችል ጉዳት

- በፍ/ህ/ቁ. 2103 መሰረት ራስን ወይም ሌላን ለማዳን በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ

- የመድን ዋስትና ካለ ካሳው እንዴት ይከፈላል? የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የመኪናው ባለቤትና መድን ገቢ ድርጅት ባልተነጣጠለ ሃላፊነት ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። መድን ዋስትና እንደ የአንድነትና ነጠላ ሃላፊነት እንዳለባቸው ዋሶች ነውን? መድን ድርጅቱ እንዲከፍል ተወስኖ ቢከሰርና ቢፈርስ እዳውንም ለመክፈል ባይችል ዋናው ባለዕዳ ያለበት ሃላፊነት?
- የፍ/ህ/ቁ. 2094 መሰረት በደረሰበት ጉዳት ጠረታ መጥሪያ የሚቀበል ሰው መጥሪያ እንደማይቀበል ሰው ሁሉ ለደረሰበት ጉዳት ኪሳራ ይጠይቃል።

  ይህ ማለት ከጠረታ ውጭ ሙሉ ጉዳት ኪሳራውን ያገኛል ማለት ነው? እንዲህ ከሆነ ከካሳ ተመጣጣኝነት መርህ አንጻር ውጤቱ?
- የፍ/ህ/ቁ. 2097(2) ቅን ልቦና - ተበዳዩ ጉዳቱን የመቀነስ ሃላፊነት አለበት ሲባል ምንድን ነው? መኪና ላይ ጉዳት ደርሶ ማስጠገን አለበት። ካላስጠገነ ለሚደርስ የጥቅም መቋረጥ ካሳ አያገኝም ማለት ነው? ማስጠገኛ ገንዘብ ባይኖረውስ? (የሰበር መዝገብ ቁጥር 54021 - ቅጽ - 11)

የፍ/ህ/ቁ. 2098 - የተበዳይ ጥፋት - ከፊል ጥፋት ካለበት ካሳው ይቀነሳል ይላል። ሙሉ ጥፋት የተበዳዩ ከሆነስ ምንም ካሳ አያገኝም ማለት ነው? በፍ/ህ/ቁ. 2081 አጥፊ ሳይሆን የመኪናው ባለቤት ሃላፊነት አለበት ከሚለው ጋር ተቃርኖ አለውን? ካለው እንዴት ይፈታል? ከፍ/ህ/ቁ. 2066(2) እና 2067(2) ጋር አብሮ እንዴት ይታያል? See የሰበር መዝገብ ቁጥር 16270 - ቅጽ 3 - የማስረዳት ሸክሙ የተከሳሽ ነው

- ሠራተኞች ጉዳት ሲያደርሱ - በፍ/ህ/ቁ. 2130 መሰረት በሌላ ሰው ተግባር ሃላፊ ስለመሆን (vicarious liability) - ሰራተኛው ባጠፋው አሠሪው ሃላፊ ይሆናል።
- ሰራተኛው በጥፋት ላይ የተመሰረተ ሃላፊነት ይኖርበታል።
- በመጨረሻ እንደ ጥፋቱ ክብደት ዕዳውን በሙሉ ወይም በከፊል አሰሪው የሚከፍልበት ስርዓት በፍ/ህ/ቁ. 2157 እና ተከታዮቹ መሰረት ተመልክ~ል።
- Ultimate liability - የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ህ/ቁ. 2082(1) እና 2156 መሰረት የመጨረሻ ሃላፊነቱ የባለንብረቱ ሳይሆን የተገለገለበት ስለሆነ ባለሀብቱ ሀላፊ አይደለም ሀላፊው የተገለገለበት ነው በማለት ወስ<ል።
- ብዙ ሰዎች ሃላፊ ሲሆኑ ካሳውን ይከፍላሉ። ነገር ግን ጥፋት ካለበት subrogate አድርገው ይካሳሉ።(የፍ/ህ/ቁ. 2155፣ 2156)

በካሳ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለማቅረብ -የፍ/ህ/ቁ. 2153 - ዳኞች ሊገምቱት የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያላግባብ በመያዝ ውሳኔ ሰጥተው እንደሆነ ወይም ሊገምቱ የሚገባቸውን ትክክለኛውን መንገድ ትተው ያላግባብ የሆነውን ያገማመት መንገድ ይዘው የተገኙ እንደሆነ... (የሰበር መዝገብ ቁጥር 53598 - ቅጽ 11)

ለህዝብ ጥቅም መሬት ስለማስለቀቅ

- አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 7 መሰረት ለከተማ ነዋሪ በመሬት ላይ የዋለው ገንዘብና የጉልበት ዋጋ - ግን በማናቸውም ሁኔታ አንድ ክፍል ቁጠባ ቤት ሊያሰራ ከሚችል ያነሰ መሆን የለበትም
- አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 8 መሰረት የገጠር መሬት በቋሚነት ለሚለቅ የዓምስት ዓመት አማካይ ገቢ በአስር ተባዝቶ

ማጠቃለያ

- ከውል ውጭ ሃላፊነት ካሳ ለማስከፈል
  1. ግልጽ ጉዳት
     - የደረሰ ጉዳት - actual damage
     - ወደፊት የሚደርስ የተረጋገጠ ጉዳት
  2. የሞራል ጉዳት ካሳ
- የካሳ ጥያቄ ክርክሮች ሲቀርቡ

  - በመጀመሪያ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 መሰረት የካሳ ጥያቄ በተከሳሽ መካድን እንደማይጠብቅ ማስታወስ ያስፈልጋል። በሌለበት የሚታይ ተከሳሽንም ውጤቱ ተመሳሳይ ነው። (የሰበር መዝገብ ቁጥር 94181 - ቅጽ 16)

  - ይህ ማለት ከሳሽ ወገን ሁልጊዜ የደረሰበትን ጉዳት ማስረዳት አለበት ማለት ነው።

- የሰው አካል ጉዳት ከሆነ ጊዜያዊ ወይም gሚ የአካል ጉዳት የሚለውን በህክምና የማረጋገጥ ሃላፊነት ፍርድ ቤቶች አለባቸው።
- gሚ የአካል ጉዳት ከሆነ ጥቅም መgረጡ በከፊል ወይም በሙሉ የሚለውን ከሰራው ባህሪ አንፃር መመርመርና በዚሁ አግባብ መወሰን ያስፈልጋል።
- ከሳሽ የሚያስረዳው ዕድሜውን፣ ስራውን፣ የተgረጠ ገቢውን፣ የዕድሜ ጣሪያውን፤
- በጉዳቱ ሰው ከሞተ ልጆቹ ወይም ባለቤቱና ወላጆቹ በህይወት ቢኖር ምን ያህል አስተዋፅኦ ሊያደርግ እንደሚችል በማስላት ሲሆን አከፋፈሉ እንደ ቀለብ በየወሩ ወይም አንድ ጊዜ ጥቅል ክፍያውን እንዲያገኙ መወሰን ይቻላል። (የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በአከፋፈሉ ላይ የተለያዬ አgም ስለያዘ ሌላ በቂ ምክንያት ከሌለለ lump sum ክፍያ የተሻለ ነው)

- በንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ የጉዳቱ መጠንና ስፋት፣ በመጎዳቱ የተgረጠ ገቢ በማስረጃ አጣርቶ መወሰን ያስፈልጋል።
- በጉዳቱ ዓይነት ወይም በሌላ ምክንያት የካሳ መጠኑ በግልጽ ማስረዳት የማይቻል ወይም ማስረጃው መጠኑን በትክክል ካልገለጸ ጉዳዩን በርትዕ መወሰን ያስፈልጋል።
- በሁሉም የክርክር ሂደቶች በተቻለ መጠን የካሳ ተመጣጣኝነትና ተመዛዛኝነት መርህን ለማሳካት ድንጋጌዎችን ከዓላማው አንፃር መተርጎም ያስፈልጋል!!!!!!!!!!!!!!!!!!

አመሠግናለሁ!